# ከዚህ በኋላ ምን እናድርግ? መልእክት ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ለአርበኞች ግንባርና ለኢሳት!

## በአስተውሎት ይነበብ!

"በኢትዮጵያ አንድነትና ህልውና ጉዳይ ላይ ለድርድር የማይቀርብ የጸና አቋም አለኝ!" ቢለንና "የጎሳ ወይም የዘውግ ፖለቲካን ጎጅነትና ጠንቀኝነት አውቃለሁ!" ብሎ ጎሰኝነትን ቢያወግዝ አምነነው ከጎኑ ቆመንለት፣ ነፍሳችንን ሰጥተንለት፣ ብዙ ተስፋ ጥለንበት የነበረው ግንቦት 7 ለዚህች ሀገርና ሕዝብ ህልውናና ደኅንነት የጸና አቋም ካላቸው ወገኖች የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ሲቦጠቡጥ፣ ታጋዮችን ሲያሰባስብ ከቆየ በኋላ እንዴትና ለምን ይሄንን የቀደመ አቋሙን አጥፎ ወይም ጥሎ የጎሳ ፌዴራሊዝምን (የራስ ገዝ አሥተዳደርን) የሚያቀነቅኑትን አካላት ተቀብሎ፣ ይሄንን የአሥተዳደር ሥርዓት ለመገንጠላቸው ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠሪያ እንደሚጠቀሙበት በግልጽ ሳይቀር ከሚያወሩ ዘውገኛ ጅርጅቶች ጋር ጥምረት ፈጠረና በፍጹም ያልጠበቅነውን ክህደት ፈጽሞ ልባችንን አደማ አንጀታችንን ቆረጠ፡፡

ለምን? እንዴት? ብለን የግንቦት 7 ኃላፊዎችን ስንጠይቅ የተጣመሯቸው ድርጅቶች ቋንቋንና ጎሳን ወይም ብሔረሰብን መሠረት ያደረገ የራስ ገዝ የአሥተዳደር ሥርዓትን የሚያቀነቅኑና ለዚህም የሚታገሉ ከሆኑ ድርጅቶች ጋር መሆኑን ጨርሶ እረስተውት "የግንቦት 7 ዓላማ ትግል ወያኔን አስወግዶ ሥልጣንን ለሕዝብ እስከማስረከብ ድረስ ነው፤ ቀጣዩን የመንግሥት አሥተዳደር ሥርዓት ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት የሚወስነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጅ ግንቦት 7 አይደለም!" ብለውን አረፉት፡፡ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ በፊት የራሳቸውን አቋም ይዘው ይሄንን አቋማቸውንም በተለያየ መንገድ በሕዝብ ላይ ለመጫን ጥረት እያደረጉ ካሉ ድርጅቶች ጋር ተጣምሮ እየሠራ እንዴት እንዲህ ዓይነት ምላሽ ሊሰጠን ይቻላል? ምን ዓይነትስ ድንቁርና ወይም ሽፍጥ ነው??

እጅግ የሚገርመው ጉዳይ ደግሞ እንዲህ ብለውን ሲያበቁ "እብለታቹህ፣ ሽፍጣቹህ፣ ክህደታቹህ ይጋለጥ!" ሲላቸው የግንቦት 7 ኃላፊዎች ሰንበት አሉና ወያኔ በኢፍትሐዊነት ለሽፍጡ፣ ለውንብድናው እንደሚያመቸው አድርጎ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይሁንታና ፈቃድ ውጪ የሸነሸነውን "ክልል" ሲል የሚጠራውን የራስ ገዝ አሥተዳደር "ይፍረስ! ብሎ ማለት ኢትዮጵያን ማፍረስ ማለት ነው! ስለሆነም አናፈርሰውም! ቁርጣቹህን እወቁት! ቢመራቹህም ዋጡት!" ምንትስ ብለውን አረፉት ግንቦት ሰባቶች፡፡
ስለዚህ የግንቦት 7 ዓላማና ትግል አሁን ያለውን የወያኔ የይስሙላ የራስ ገዝ አሥተዳደር በትክክል ተፈጻሚ አድርጎ የወያኔውን ኦሕዴድ በኦዴግ/ኦነግ፣ ደሕዴንን በሲዳማ ነጻ አውጭ፣ ሌሎቹን የወያኔ/ኢሕአዴግ ተጣማሪዎችንም በሌሎቹ የራሱ ተጣማሪዎቹ ተክቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ የግጭትና የቀውስ አዙሪት ውስጥ ከቶ ኢትዮጵያ አስከመበታተን የምትደርስበት የቀውስ ዋዜማ ድረስ ነው ማለት ነው የሚታገለውና ዓላማው፡፡ እጅግ በጣም ነው የምናዝነው!!!

እርግጥ ነው ሕዝብ ያለማንም ጣልቃገብነት አስገዳጅነትና አታላይነት ወይም አሳሳችነት የሀገርንና የሕዝቧን ጥቅም ታሳቢ በማድረግ በራሱ እንዲወስን እስከተፈቀደለት ጊዜ ድረስ የሚወስነው ውሳኔ ምንጊዜም ትክክልና ጠቃሚም ነው! ችግሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን ያለበት ሁኔታ ያለማንም ጣልቃገብነት፣ ወትዋችነት፣ አሳሳችነት በራሱ እንዲወስን የሚችልበት ሁኔታ ላይ ነው ወይ ያለው? አንድነቱን፣ ትስስሩን፣ ፍቅሩን፣ ዝምድናውን ሊያጠፉ፣ ሊያፈርስ፣ ሊያደፈርስ የሚችል ወሬ ያውም የፈጠራና መርዘኛ ወሬ ለሆዳቸው እራሳቸውን ለጠላት በሸጡ፣ ለዕኩይ ጥቅማቸው ባደሩ፣ ፍጹም ኃላፊነት የሚባል ነገር በማይሰማቸው በወያኔና በሌሎች የጥፋት ኃይሎች እየተነዛለት በግድ እንዲቃቃር፣ እንዲለያይ፣ በጠላትነት እንዲተያይ እየተገደደ፣ እየተዋከበ፣ እየተገፋ ያለበት ሁኔታና ከዚህም የተነሣ አንድነቱ፣ ፍቅሩ፣ የደም ትስስሩ፣ ዝምድናው የላላበት የደፈረሰበት ሁኔታ አይደለም ወይ ያለው?

በአሁኑ ጊዜ ነገሮች እንዲህ ተሳክረው፣ ተበጥብጠው፣ ደፍርሰው፣ ጎሽተው ባሉበት ሁኔታ ለህልውናውና ለደኅንነቱ የሚበጅ ትክክለኛና ነፃ የሕዝብ ውሳኔ ማግኘት የሚቻል ሆኖ ነው ወይ "ሕዝብ

ይወስናል!" የሚባለው??? ነው ወይስ ውጤቱ የጥፋት ኃይሎቹ ፍላጎት እንደሚሆን ታውቆ ሽፍጥ መሸፈጡ ነው?

የጎሳ ፖለቲካ (እምነተ አሥተዳደር) ወይም ጎሳን ብሔረሰብንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ የራስ ገዝ አሥተዳደር ምን ያህል ጠንቀኛ አደገኛና ኋላቀር ወይም ያልሠለጠነ እንደሆነ ከዚህም የተነሣ በሠለጠነው የዓለማችን ክፍል የማይሠራበትና የተወገዘ መሆኑን ለዓመታት በተለያዩ ጽሑፎቸ ሳስረዳ የቆየሁት ጉዳይ ስለሆነ የሩቆቹን ትተን ከቅርቦቹ ሁለቱን ልጠቁማቹህና አንዱ "የሀገራችንና የሕዝቧ ህልውና መቀጠል ካለበት በዘውገኛ ፖለቲከኞች ላይ ሰይፋችንን እናንሣ!" የሚለው ሲሆን ሌላው ደግሞ "የአማራ ሀገር አቀፍ የፖለቲካ ድርጅት የመመሥረት አስፈላጊነትና ዓላማ አደረጃጀቱ!" በሚሉት ጽሑፎቸ ጉዳዩን ለሁሉም የአንባቢ ዓይነት ሊገባ በሚችል ሁኔታ በሚገባ ያብራራሁት ጉዳይ ነውና ነገር ላለማስረዘም ዛሬ ላነሣው ወደ ፈለኩት ነጥብ ልለፍ፡፡

በዚህ ጽሑፍ ላነሣው የፈለኩት ጉዳይ እንግዲህ የግንቦት 7 አቋምና ዓላማ በዚህ ደረጃ ግልጽ ከሆነ፤ ወገን ሆይ! አርጅቶ የደከመ ጉልበት የያዘውን ጠንቀኛ የጥፋት ኃይል ወያኔን ሸኝተን አዲስ ጉልበት በያዘ ሌላ ጠንቀኛ የጥፋት ኃይል ተክተን እንደገና በአዲስ ጨቋኝ ለመረገጥና ለመፈራረስ ለመበታተን ካልሆነ በስተቀር ከዚህ በኋላ ግንቦት ሰባትን የምንደግፍበት የምንረዳበት ምክንያትና ዓላማ ምንድን ነው???

ምንም እንኳ እስከዛሬ ለግንቦት ሰባት ያደረግነው ሁሉን አቀፍ ድጋፍ የሚያስቆጭ ቢሆንም ብዙ ሳንከስር በጊዜ ራሱን እንዲህ ግልጽ ማድረጉ ግን መልካም ነውና ለትግል ያለን መነቃቃት ቅንጣት ታክል መብረድ ሳይኖርበት ሁሉን ዓይነት ድጋፍ ትብብራችንን የሀገራችንን አንድነትና ህልውና ፈጽሞ ለድርድር ለማያቀርቡ በትግል ሜዳ ላይም በአሁኑ ሰዓት አስደናቂ ድል እያስመዘገቡ ላሉ አርበኞች በማድረግ ነጻነታችንን ለመቀዳጀት እንድንተጋ አጥብቄ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡ በዚህም መሠረት መልእክቴን ማስተላለፍ ልጀምርና፡-

## ለአርበኞች ግንባር፡-

ባለኝ መረጃ የአርበኞች ግንባር ታጋዮችና ኃላፊዎች ግንቦት ሰባት ከዘውገኛ ጅርጅቶች ጋር የፈጠረውን ጥምረት አርበኞች ተቃውመዋል፡፡ ሲጀመርም ቢሆን መላ ታጋዩ በተገኘበት በጉዳዩ ላይ ግልጽ ማብራሪያ ቀርቦ ተመክሮ ተዘክሮበት አንድ አቋም ለመያዝ ወይም የማይስማማ ካለም ከያዘው አቋሙ ጋር የመለየት ዕድል እንዲሰጠው ባልተሞከረበት ሁኔታ ግንቦት 7 በኃላፊዎቹ ግብታዊ ውሳኔ በአርበኞች ግንቦት 7 ስም ጥምረቱን መፈረሙ እጅግ ስሕተት ነው ብቻ ሳይሆን የለየለት አንባገነናዊ ድርጊትም ነው፡፡ እንግዲህ የግንቦት 7 አቋምና ዓላማ ይሄ መሆኑ ከታወቀ የአርበኞች ግንባር ኃላፊዎችና ታጋዮች እንዲሁም ይሄንን የግንቦት ሰባትን ክህደት የምትቃወሙ የግንቦት 7 ታጋዮች ጭምር ከዚህ በኋላ ከግንቦት 7 ጋር ልትቀጥሉ የምትገደዱበት ምክንያትና ዓላማ ፈጽሞ የለምና ሁኔታው እንዳመቻቹህ ግንቦት ሰባትን በመለየት የከፋኞችን አርበኞች እንድትቀላቀሉ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

ምክንያቱም ከዚህ በኋላ ይሄንን አቋም ይዛቹህ በባሕረ ምድር (ኤርትራ) ደኅንነታቹህ ተጠብቆ መቆየት የምትችሉበት ዕድል የላቹህምና፡፡ ነገሩ አስቀድሞ ተበላሽቷል፡፡ ያላቹህበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ግንቦት 7 ለፈጸመው ክህደት የልባቹህን በልብ አድርጋቹህ ምንም ዓይነት የተቃውሞ ምላሽ ባታንጸባርቁ ኖሮ ምቹ ሁኔታ እስከታገኙ ወይም የሀገራቹህን መሬት እስክትረግጡ ድረስ ለጥቃት ሳትጋለጡ ተመሳስላቹህ መቆየት ትችሉ ነበር፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ ግን ይህ ዕድል ያመለጠ በመሆኑና ከመሀላቹህ ጥቂት የማይባሉትም በመቃወማቸው ምክንያት ለእስራት በመዳረጋቸው፣ ምናልባትም አንዳንዶቹ ለሞት የተዳረጉ ሊኖሩ እንደሚችሉ፣ የተቀራቹህትም ከዚህም በኋላ ተለቅማቹህ ከመፈጀትና በግዳጅ የእነሱን አቋም ተሸክማቹህ ለጥፋት ዓላማቸው አባሪ ከመሆን ውጪ ሽአቢያ ከያዛቹህት አቋማቹህ ጋራ ሊያስተናግዳቹህ የሚችል ባለመሆኑ እዚያ መቆየታቹህ ፋይዳ የለውምና እዚያ በከንቱ ከምታልፉ የከፋኝ አርበኞችን ተቀላቅላቹህ በጠላት ላይ ጥቃት በማድረስ የሚሠዋው ቢሠዋ የሚተርፈው ተርፎ የሀገራችንንና የሕዝባችንን ነጻነት እውን ለማድረግ መጣሩ የተሻለ ነውና ይሄንን ለማድረግ ትተጉ ዘንድ መልእክቴን ማስተላለፍ እወዳለሁ፡፡

## ለኢሳት፡-

እስከ አሁን ባለው ጊዜ ኢሳት ለግንቦት 7 ሁነኛ ልሳን ሆኖ ሲያገለግል መቆየቱ ይታወቃል፡፡ ኢሳት

ለግንቦት 7 እንዲህ መሆኑ ግንቦት 7 የአንድነት ኃይል ነኝ ይል ስለነበረ የሚገባ እንጅ የሚኮነን አልነበረም፡፡

ኢሳትን ሳስብ እጅግ የሚገርመኝና "ለመሆኑ ኢሳት እንደ አንድ የብዙኃን መገናኛ ኤዲቶሪያል ፖሊሲ (የአርትኦት መመሪያ) አለው ወይ? ሥራ ሲሠራ ዓላማና ግብ ይዞ ነው ወይስ ዝም ብሎ በእውር ድምብሱ ነው የሚሠራው?" የሚያሰኘኝ ጉዳይ አለ፡፡ ይሄን ጉዳይ በተመለከተ ኢሳት አሠራሩን ዘመናዊና ደረጃውን የጠበቀ ያደርግ ዘንድ የሚረዳውን ጽሑፍ ከዚህ ቀደም ጽፌ እንደነበር ይታወሳል፡፡ የሚገርመኝና ግራ የሚያጋባኝ ጉዳይ ምንድን ነው? ለምሳሌ እንደምታዩት ኢሳት ለወልቃይት ሕዝብ የአማራ ማንነት ንቅናቄ ጥሩ ሽፋን ይሰጣል፡፡ ይሄ ጥሩ ትክክለኛና የሚደገፍም ነው፡፡ የሚገርመውና ግራ የሚያጋባው ነገር ግን ኢሳት የዚህን ድርጊቱን አፍራሽ ወይም ተቃራኒ ተግባርም የሚፈጽም መሆኑ ነው፡፡

እንዴት? ብትሉ እንደምታውቁት ኢሳት ለትሕዴን (ለትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) ወይም ለደሚሕት የአየር ሰዓት ሰጥቶ ደምሒት በተሰጠው የአየር ሰዓት የራሱን ዓላማና አቋም እንዲገልጽ እያደረገ ነው፡፡ ኢሳት ራሱም ስለ ደሚሕት በርካታ ፕሮፖጋንዳ (ልፈፋ) እየሠራ ይሄንን የጥፋት ኃይል ለማደርጀት የበኩሉን አስተዋጽኦ ሲያበረክት ቆይቷል፡፡ እንቆቅልሹ እንግዲህ ያለው እዚህ ላይ ነው፡፡ ደሚሕት ወልቃይትን በተመለከተ ከወያኔም የባሰ ጽንፈኛ አቋም ያለው ጠባብ የጥፋት ኃይል መሆኑ ነው፡፡

ኢሳት ለደሚሕት የአየር ሰዓት ሊሰጥ እንደሆነ ገና ሲያስታውቅ በፍጹም እንዳያደርገውና ይህ ድርጊቱ "ለሀገር ላበረክተው እፈልጋለሁ እተጋለሁ!" ከሚለው አቋሙ ጋር የሚጋጭ የሚጻረር እንደሆነ ከደሚሕት መግለጫ መረጃ በመጥቀስ በወቅቱ ጽሑፍ መጻፌ ይታወሳል፡፡ ደሚሕት ወያኔን ተቃውሜ ወጣሁ የሚልበት ዋነኛ ምክንያቱና ዓላማው "ወያኔ በረሀ እያለ ለትግራይ ሕዝብ የገባውን ቃል ሊፈጽም አልቻለም!" በሚል ቅሬታ እንደሆነ ተናግሯል፡፡ ይህ ትሕዴን "ወያኔ ለትግራይ ሕዝብ  የገባውን ቃል ሊፈጽም አልቻለም እኔ እፈጽመዋለሁ!" ከሚላቸው ቃል የተገቡ ጥቅሞች አንዱ "ትግራይን በወሎ በኩል እስከ አለውኃ ድረስ በጎንደር በኩል ወልቃይትን ብቻ ሳይሆን ጠለምትን ይዞ ደባርቅ ድረስ፣ በአፋር በኩል ከነባ ድረስ አሰፋለሁ!" የሚለው አንዱ ነው፡፡

እና ታዲያ እንግዲህ ኢሳት ለሁለቱም ተቃራኒ ዓላማና ግብ ላላቸው አካላት ድጋፍና አዎንታዊ ሽፋን ሲሰጥ በማየታችን "ኢሳት ዓላማና ግብ አልባ ነው! የሚያደርገውንም አያውቅም!" ብለን ብናማው እንዴት ነው ሐሜታችን አግባብ አይደለም ሊባል የሚችለው?

በነገራችን ላይ ይሄንን ስሕተት የሚሠራው ኢሳት ብቻ አይደለም፡፡ ግንቦት ሰባትም እንደምታስታውሱት ወያኔ ለወልቃይት የአማራ ማንነት ሕጋዊ ጥያቄና ንቅናቄ አንባገነናዊ የሆነ፣ ለሰልፍ የወጣን ሰላማዊ ሕዝብ በሩምታ ቶክስ እስከመፍጀት የደረሰ የኃይል ምላሽ በሰጠ ጊዜ ግንቦት 7 ምን እያለ ከዚህ ሕዝባዊ ንቅናቄ ጎን እንደሆነና ድጋፍ በመስጠትም አጋርነቱን ይገልጽ እንደነበረ የምታስታውሱት ነው፡፡ በጎን ደግሞ የዚህ ንቅናቄ ተጻራሪ ከሆነው ደሚሕት ጋር ጥምረት ፈጥሯል ካልተዋሐድን እያለም እየወተወተ ይገኛል፡፡ እና አሁን እነኝህ አካላት የሚሠሩትን ያውቃሉ?

ኢሳት እንደማንኛውም የብዙኃን መገናኛ ተቋም ከማንም ያልወገነ ገለልተኛ አቋም ያለው (እንዲህ ዓይነት የብዙኃን መገናኛ በዓለማችን ያለ ከሆነ ማለቴ ነው) እንዲህ ዓይነት የብዙኃን መገናኛ ቢሆን ኖሮ ይሄንን ሐሜት ለመሰንዘር ባልቻልን ነበር፡፡ ኢሳት ግን እሱም እንደሚለው የሚሠራው የቆመውና የሚታገለው በአንባገነኑ ወያኔና በአጋር ቢጤዎቹ ግፍ የደረሰበትንና እየደረሰበት ያለውን የኢትዮጵያን ሕዝብ በመደገፍ በማስተባበር ነጻ ሊወጣ የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሚሠራ፣ ከሕዝብ የወገነ የሕዝብ ተቋም እንደሆነ በመናገሩ ነው ይሄንን ክስ ለማቅረብ የተገደድኩት፡፡

ኢሳት ይህን የእውር ድምብስ አኪያሔዱን እስካላቆመ ጊዜ ድረስ "ለሀገር አበረክታለሁ!" የሚለውን ፈጽሞ ሊያበረክት እንደማይችልና ጭራሽም ሊመለስ በማይችልበት የጥፋት መንገድ ነጉዶ የአዳዲስ አጥፊዎቿ ልሳንና መጠቀሚያ ሆኖ ሀገርና ሕዝብን መቀመቅ የያወርድ እንዳይሆን ከባድ ሥጋት አለኝ፡፡

ኢሳትንና አኪያሔዱን የሚደግፈውን ማንኛውንም አካል ማስገንዘብ የምሻው ዐቢይ ቁምነገር ቢኖር የጥፋት ኃይሎች ለማስመሰልና ለመደለል ሆን ብለው በሚናገሩት ፕሮፖጋንዳ (ልፈፋ) አጉል ተስፋ እየሰነቀና እነሱን ወደቀና መንገድ መመለስ የሚችል እየመሰለው የቱንም ያህል በሆደሰፊነትና በሰፋ ትዕግሥት ለማስተናገድ ቢጥር ትሕዴንን ጨምሮ አነግንና አነግን የመሰሉትን የጥፋት ኃይሎችን ሁሉ በምንም ተአምር ከጥፋትና ዕኩይ ዓላማ አስተሳሰባቸው ሊያወጣቸው፣ ሊመልሳቸው ለዚህች ሀገርና ለሕዝቧ ጠቃሚ ኃይል

ሊያደርጋቸው ከቶውንም እንደማይችል መቶ በመቶ እርግጠኛ ሆኘ ልነግረው እወዳለሁ፡፡

ምክንያቱም እነኝህ የጥፋት ኃይሎች ለጥፋት ተልእኳቸው ስላልተመቸ ብቻ እውነትን፣ ታሪክን፣ መረጃን ሸምጥጠው የሚክዱ፣ ለእነሱ የጥፋት ተልእኮ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ሲሉ ደግሞ የሌለና ያልነበረን ነገር በመፍጠር እውነት አስመስለው የሚያወሩ፣ ሞራላዊ (ቅስማዊ) እና ሰብአዊ ዋጋቸው እጅግ የወረደ፣ ሥነ ልቦናቸው የተቃወሰ፣ ሰብእናቸው የተመረዘ፣ ለእውነታ ለአመክንዮ ለሞራል ድንጋጌዎች መገዛትና በእነሱም መዳኘት ፈጽሞ የማይፈልጉ የጥፋት መንጋ መሆናቸውን በሚያደርጉት ሁሉ አረጋግጠውልናልና፡፡ ይህ ሁኔታቸው ጠላት ተወዶ ተፈልጎ እንደማይፈጠርና ሊፈጠር በማይገባበት ሁኔታ ከተፈጠረ በኋላም እነኝህን ዕኩይ አስተሳሰብ ተጠቅጥቀው የተሞሉ የጥፋት ኃይሎችን ባጭር ታጥቆ ያለማጥፋት በስተቀር ሌላ መፍትሔ እንደሌለ የሚያረጋግጥ ጉዳይ ነው፡፡

ኢሳትና የኢሳትን አኪያሔድ የሚደግፉ ሁሉ ልብ ብለው ነገሩን ቢያጤኑት ከእስካሁን ድካማቸው እነኝህን የጥፋት ኃይሎችና በስውርና በግልፅ የሚደግፏቸውንም ኢምንት እንኳን ፈቀቅ ሊያደርጓቸው እንዳልቻሉ ሊረዱና ከንቱ ድካም እየደከሙ እንደሆነ ሊያውቁ በቻሉ፡፡ በአንፃሩ ግን የጥፋት ኃይሎቹ ከትናንት ዛሬ ይበልጥ አቅም እያገኙና እየደረጁ ነው ሊመጡ የቻሉት፡፡

እንዳልኩት ሁሉም የሚስማማ የሚጣጣም ቢሆንና ጠላት ወይም ጽንፈኛ ተቃራኒ ሐሳብ ያለው ኃይል ባይኖር መልካም ነበር፡፡ እንዳይኖር መሥራቱም እንዲሁ፡፡ የሚያሳዝነው ነገር ግን የፈለገ ነገር ቢደረግ ጠላት እንዳይፈጠር እንዳይኖር ማድረግ የማይቻል መሆኑ ነው፡፡ በዓለማችን ጠላት የሌለውና ጠላት እንዳይፈጠርበት እንዳይኖርበት ማድረግ የቻለ ሀገር የለም፡፡ ጠላት ቢኖርበትም ጠላቱ የደኅንነቱ፣ የሰላሙ፣ የህልውናው አደጋ እንዳይሆን ማድረግ የቻሉ ሀገራት ግን አሉ፡፡ እውነታው ይሄና ይሄ ብቻ ነው፡፡ በከንቱ ድከሙ ካላለን በስተቀር፣ ስትንገላጀጁ የአውሬ ሲሳይ ሁሉ ካላለን በስተቀር በምንም ተአምር ጠላት እንዳይኖርብን ማድረግ አንችልም፡፡ ልናደርግ የምንችለው ጠላቶቻችንን የህልውናችን፣ የደኅንነታችን፣ የሰላማችን አደጋና ሥጋት እንዳይሆኑ ነው ልናደርግ የምንችለው፡፡

ኢሳትና የኢሳትን አኪያሔድ የሚደግፍ አካል ሁሉ የቱንም ያህል ይቅር ባይ፣ ታጋሽና ሆደሰፊ ቢሆን፤ በምንም ተአምር የክርስቶስን ያህል ይቅር ባይ፣ ታጋሽና ሆደሰፊ... ሊሆን አይችልም! ኢሳትና ተከታዩ የክርስቶስ ይቅር ባይነት፣ ታጋሽነትና ሆደሰፊነት አይሁድን ከጥፋት መንገዳቸው እንዳልመለሰ አውቆ ከዚህ በኋላ ያለውን ጊዜ፣ ጉልበት፣ አቅሙን፣ ገንዘቡን ወዘተርፈ ከአይሁድ የከፋ እኪተኛና እኩይ ልብ ባላቸው የጥፋት ኃይሎች ላይ በከንቱ ከማፍሰስ ከማባከን ተቆጥቦ ጊዜውን አቅሙን ሁለነገሩን በአንድነት ኃይሉ ላይ ብቻ አተኩሮ በማፍሰስ ቢሠራ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ አይደለም ለአፍሪካ የሚበቃ ጠንካራ የለውጥ ኃይል መፍጠር ይችላልና ለዚሁ እንዲተጋ፣ ከንቱ ሆኖ ከንቱ አድርጎን እንዳይቀር አጥብቄ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

ይሄንን ለማድረግ ይሚችል የቴዎድሮስ መንፈስና ዓላማ የተዋሐደው ቆራጥ ሕዝብ አለንና ከተሠራበት ይሄንን የሀገር መድኅን የሆነን ኃይል መፍጠሩ በጣም ቀላል ነው፡፡ ቴዎድሮስ ጠላቶቹ ምን ቢበዙ ሁሉንም መደምሰስ መቻሉን፣ ዓላማው ምን ከባድና አስቸጋሪ ቢሆን ማሳካቱን ልንዘነጋ አይገባም፡፡ የፈሰሰ ሐሞታችንን እናጠንክር! ባጭር ታጥቀን እንነሣ! መፍትሔው ይሄና ይሄ ብቻ ነው እንጅ "ሰይጣንን መልአክ አድርገን ከጎን ማሰለፍ እንችላለን!" የሚለው ምኞት ከንቱ ቅዠትና የሚያስበላ ቂልነትም ነው፡፡ ክርስቶስ የሱ ይቅር ባይነት፣ ታጋሽነትና ሆደሰፊነት አይሁድን ከጥፋት መንገዳቸው እንደማይመልስ እያወቀም የሆነውን ሆኖ ማለፉ አምላክነቱ ስላስገደደው ነው፡፡ ኢሳትና መሰሉ ግን አምላክ አይደለምና ይሄንን ቢያደርግ ከመክሰርና ሀገርና ሕዝብንም ከማክሰር ውጪ የሚያተርፈውና ለሀገር የሚጠቅመው አንዳችም ነገር አይኖርም፡፡

በመሆኑም ኢሳት ከዚህ በኋላ ዓላማውና የሚታገለውም ዕኩይ ግብ የሸመቁትን ጠባብ ዘውገኞችን ተሸክሞ ለስኬታቸው ማድረስ ለሆነውና ወደ ጥፋት ኃይሎች ጎራ ለተቀላቀለው ግንቦት ሰባትም መጠቀሚያ ከመሆን መቆጠብ ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ እንደማየው ግን ኢሳት ይሄን ያደርጋል ብሎ ተስፋ ለማድረግ በጣም የሚያስቸግር ይመስለኛል፡፡ ሁሉንም ሰንብተን ማየት ይኖርብናልና ጥቂት ታግሰን ማየት ነው፡፡

ከሀገር ውጪ ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን፡-

ከሀገር ውጪ ያለኸው የሀገርህና የሕዝቧ ህልውናና ደኅንነት እንቅልፍ የሚነሳህ፣ የሚያንገበግብህ ወገን ሆይ! ግንቦት 7 ባያቹህትና በሰማቹህት መልኩ ክህደት የፈጸመብንና ወደ ጠላትነት ወይም የጥፋት ኃይልነት የተለወጠ በመሆኑ ከዚህ በኋላ ምንም ዓይነት ድጋፍና እርዳታ ወይም ትብብር ለግንቦት 7 ማድረግ በፍጹም

ተገቢ አይደለም፡፡ ለኢሳት የምታደርገው ድጋፍና እርዳታም ኢሳት ከላይ የገለጽኩት ሁሉ የማይገባው፣ የማይነቃና መጠቀሚያ ሆኖ ልቀጥል የሚል ከሆነ ኢሳትን ቀጥ አድርገህ የያዝከው አንተ በመሆንህ ድጋፍህን ወዲያውኑ አቁመህ ሌላ ለዚህች ሀገርና ለሕዝቧ የቆመ የገባው የሕዝብ የብዙኃን መገናኛ በማቋቋም የዜግነት ኃላፊነትህንና ግዴታህን እንድትወጣ ወገናዊ ጥሪየን ላቀርብ እወዳለሁ፡፡

ወገን ሆይ! አጥብቄ ላሳስብህ የምሻው ጉዳይ ቢኖር ግን ግንቦት 7 ከሸፈ ማለት በፍጹም በፍጹም ትግል አለቀለት ማለት አይደለምና ትግልን የመደገፍና በትግል የመሳተፍ መነቃቃትህና ወኔህ ቅንጣት እንኳ ሳይበርድ መሬት ላይ የሚታይ ውጤት እያስመዘገቡ ያሉትን እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች የከፋኝ አርበኞችን በመርዳት በቅርብ ርቀት ላለችው ነጻነትህ አስተዋጽኦህን ተግተህ እንድታበረክት ነው፡፡

ይህ የከፋኝ አርበኞች ኃይል በተሻለ እልህ ንቃትና ወኔ በጀግንነት ከጠላት ጋር እየተናነቀ ያለ የወገን ኃይል በመሆኑ ትግልን ሀ ብሎ እንደገና ወደመጀመር መውረድ ሳያስፈልገን ለነጻነታችንና ለህልውናችን መታገል እንችላለንና በፍጥነት የከፋኝ አርበኞችን በማጠናከሩና ትግሉን በፖለቲካ (እምነተ አሥተዳደር) ድርጅት ደረጃ በማደራጀቱ ረገድ በተለይም ምሁራኑ በፍጥነት ትረባረቡ ዘንድ አጥብቄ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡ ይሄንን ጉዳይ ሳስብ የምሁራኑ ፍዘት እጅግ እጅግ እጅግ ይገርመኛል፡፡ እዚህ ሀገር ቤት ሕዝብ እንዲህ በወያኔ እየተቀላንና እየተጨፈጨፍን እንዴትና ለምንስ ነው በዚህ ደረጃ ልትፈዙና ልትደነዝዙ የቻላችሁት???

አሁን ያለንበት ወቅት ወያኔ ለ 26 ዓመታት የነዛው የጠባብነት፣ የጎጠኝነት፣ የፀረ አንድነትና የፀረ ኢትዮጵያ የጥፋት መርዘኛ ስብከት ውጤት አሁን መጨረሻ ላይ አማራ ላይም ደርሶ የዚህ የጥፋት ስብከት ፍሬ የሆኑ ኢትዮጵያንና አንድነትን የጣሉ፣ ከአማራነት የጨነገፉ፣ ስለሚያወሩት መገንጠልና ውጤቱ አዋጭነት ወይም አጥፊነት በተጨባጭ የሚያውቁት ኢምንት ነገር እንኳን የሌላቸው የወያኔ ተቀጽላ የጥፋት ኃይሎች የወጡበት ጊዜ በመሆኑ የተነቃቃው የሕዝባችን ትግል በእነኝህ የወያኔ ተቀጽላዎች እንዲኮማሸሽ ዕድል ላለመስጠት ከፍዘት ድንዛዜያቹህ ቶሎ በመንቃት አስቸኳይ አጠቃላይ የወገን የስብሰባ ጥሪ በማድረግ ፈጥናቹህ የዚህን ድርጅት ምሥረታ እውን በማድረግ ድጋፍ ትብብራቹህን ለከፋኝ አርበኞች ታደርጉ ዘንድ አጥብቄ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

ይህ በቴዎድሮስ መንፈስ የሚመራ፣ የቴዎድሮስን ዓላማ የታጠቀ ኃይል እንደ ሠለጡኑ ሀገራት ሁሉ የሀገርና የሕዝብ ሥልጣኔ፣ ብልጽግና፣ ሰላም፣ ደኅንነትና ህልውና ጠንቅ የሆነውን የጎሳ ፖለቲካን (እምነተ አሥተዳደርን) ከዚህች ሀገር ጠራርጎ አጥፍቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከላይ እስከ ታች ራሱ በሚመርጣቸው መሪዎቹ የሚተዳደርባት ፍጹም ዲሞክራሲያዊት (መስፍነ ሕዝባዊት) የሆነች ሀገርን ይመሠርታል!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com